በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የቅዱሳን አማላጅነት - ሦስተኛ ሳምንት


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon3@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## መጋቢት ፳ ቀን ፳፻፱ ዓ.ም.

# <u>አማላጅነት</u>

- *<u>ገላ 6:2</u>* "ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።" **እንደተባለ የጌታችንን ሕግ የምንፈጽምበት ነው፡፡**
- **በምድር ያለን ክርስቲያኖች ይልቁኑ ይህን ዓለም ንቀው የሚኖሩት በምድር ስላሉት ስለሌሎቹ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያሉ፡፡**
- **ቅዱሳን ስለ እኛ ይጸልዩልን ዘንድ አማላጅነታቸውን እንጠይቃለን፡፡**
- **ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩትም በድካማቸው የተነሳ ዳግመኛ ሞት እንዳያገኛቸው መጸለይ በጥንት ቤተ ክርስቲያን የነበረ ነው፡፡** "ጌታ ለሄኔሲፎሩ ቤተ ሰዎች ምሕረትን ይስጥ፥ ብዙ ጊዜ አሳርፎኛልና፤ በሰንሰለቴም አላፈረበትም፥ ነገር ግን በሮሜ ባደረ ጊዜ ፈልጎ ፈልጎ አገኘኝ፤ በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው፤ በኤፌሶንም እንዴት እንዳገለገለኝ አንተ በደኅና ታውቃለህ።"
*<u>ካል ጢሞ 1:16-18፡፡</u>*

## *<u>ለምልጃ ትምህርት ምሳሌ የሚሆኑን፡-</u>*

1. **አባታችን አብርሃም ሎጥንና ቤተሰቡን ከባርነት ታድጎታል፡፡** "አብራምም የሰዶምን ንጉሥ አለው። ሰማይንና ምድርን ወደሚገዛ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ አድርጌአለሁ" *<u>ዘፍጥ 14፡፡1-23፡</u>*
2. **ነቢዩ ሙሴ ስለ ሕዝቡ አማልዷል፡፡** *<u>ዘጸአ 32:31-32፡፡</u>*

3. **ቅዱስ ጴጥሮስ በእስር ቤት በነበረበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ስለርሱ አብዝታ ትጸልይ ነበር፤ የታደገውም መልአከ እግዚአብሔር ነበር፡፡** "ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር። 12 6 ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ፥ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፤ ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው ወኅኒውን ይጠብቁ ነበር። 12 7 እነሆም፥ የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ፤ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና። ፈጥነህ ተነሣ አለው። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ። 12 8 መልአኩም። ታጠቅና ጫማህን አግባ አለው፥ እንዲሁም አደረገ። 12 9 ልብስህንም ልበስና ተከተለኝ አለው። ወጥቶም ተከተለው፤ ራእይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደ ሆነ አላወቀም። 12 10 የመጀመሪያውንና የሁለተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ፤ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው፤ ወጥተውም አንዲት ስላች አለፉ ወዲያውም መልአኩ ከእርሱ ተለየ። 12 11 ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ፡- ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ። 12 12 ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ።" *<u>የሐ ሥራ 12:5-12፡፡</u>*

# አማላጅነት

**እግዚአብሔር እርስ በርስ በጸሎት ስለመተሳሰብና፣ ስለ አማላጅነትና ስለፈቃዱም አስተምሮናል፡፡**

- “በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ። አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ፥ ጆሮቼም ያደምጣሉ። አሁንም ስሜ ለዘላለም በዚያ ይኖር ዘንድ ይህን ቤት መርጫለሁ ቀድሻለሁም ዓይኖቼና ልቤም ዘወትር በዚያ ይሆናሉ።” ***ካል ዜና 7፡14-15፡፡***

- “ቅጥርን የሚጠግንን፥ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፥ ነገር ግን አላገኘሁም። ስለዚህ ቍጣዬን አፈሰስሁባቸው፥ በመዓቴም እሳት አጠፋኋቸው መንገዳቸውንም በራሳቸው ላይ መለስሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡፡” ***ሕዝ 22፡30-31፡፡***

- “እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።” ***ካል ጢሞ 2፡1-2፡፡***

- “ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር። ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል። እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።” ***ያዕ 5፡13-16፡፡***

- “ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይለምኑ ነበር፡፡” ***ካል ቆሮ 8፡4፡፡***
- “በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።” ***መዝ 31፡18፡፡***
- “ኃጢአተኞችን ክፋት ይገድላቸዋል ጻድቃንንም የሚጠሉ ይጸጸታሉ።” ***መዝ 34፡21፡፡***

- “የባሪያዎችህንም በድኖች ለሰማይ ወፎች መብል አደረጉ፥ የጻድቃንህንም ሥጋ ለምድር አራዊት ደማቸውንም በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደ ውኃ አፈሰሱ፥ የሚቀብራቸውም አጡ።” ***መዝ 78፡2-3፡፡***

- **በቅዱስ መጽሐፋችን ጻድቃን 89 ጊዜ፣ ጻድቅ 151 ጊዜ፣ ቅዱሳን 148 ጊዜ፣ ምርጦች 5፣ እናቱ 141 (በሐዲስ ኪዳን 39ና በብሉይ 102) ጊዜ የተጠቀሱት ለከንቱ ነውን?**

# አማላጅነት

1. ***በዘዳግም 18፡10-12*** "ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ፥ ምዋርተኛም፥ ሞራ ገላጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቍልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ።" **ይላልና የቅዱሳን አማላጅነት ኃጢአት ይመስለኛል?**

   - **ቅዱስ መጽሐፍ ልክ *በ1ኛ ሳሙ 28* ንጉሥ ሳኦል እንዳደረገው ሙታንን መሳብን ኃጢአት እንደሆነ ነግ ሮናል፡፡ ጌታችን በደብረ ታቦር ከሙሴና ከኤልያስ ጋር መነጋገሩ ግን ሙታንን መሳብ አልነበረም፡፡ *ማቴ 17፡1-5፡፡* ልበ አምላክ ዳዊት የሰማይ መላዕክት** "ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥ የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ። ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።" ***መዝ 102፡20-21፡፡*** **ብሎ መጠየቁ ሙታንን መሳብ አልነበረም፡፡ እኛም ቅዱሳንን ጸሎታቸውን መሻታችን ሙታን መሳብ አይደለም፡፡**

2. **በሥራ ገበታዬ አለቃው ወዳጄ ሆኖ ማነጋገር ስችል ለአንድ ተላላኪ ጉዳዬን ለምን እሰጣለሁ? መጽሐፍ ቅዱስስ አንዱ አስታራቂ ጌታ ነው ይል የለ? ቅዱሳኑ ለምን ያስፈልጉናል?**

   - **በሰማይ ያሉትን ቅዱሳን መጠየቅ ከሌለብን በምድር ያሉትም ጸልዩልን ብለው የሌላውን ጸሎት መፈለጋቸው ትክክል ሆኖ ሊገኝ አይችልም፡፡ አንድ ሰው ሌላውን ይጸልይለት ዘንድ የሚጠይቀው እግዚአብሔር ሩቅ ስለሆነ ወይም ስለማይሰማንም አይደለም፡፡ ይልቁኑ ርኅራኄው የማያልቅ እግዚአብሔር በአንዱ በክርስቶስ ባለን አንድነት አንዱ አካል ወደ ሌላው ይጸልይ ዘንድ ፈቃዱ ሆነልን፡፡** "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለችና።" **ይህም ዕድል ታላቅ ዕድል ነው፡፡ ያዕ 5፡16፡፡ በሰማይ ያሉ ቅዱሳንና መላዕክት ደግሞ ያለምንም ጥያቄ ጻድቃን እንደሆኑ ባለፉት ሁለት ሳምንት ትምህርቶች ተረድተናል፡፡**

   - **ቅዱስ መጽሐፍ የሚያስፈልገንን ሁሉ እግዚአብሔርን እንድንጠይቅ ከመንገር ጋር እኛ የቅዱሳንን ጸሎት ይጠይቅ ዘንድ ያስተምረናል፡፡** "የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸውና። … ጻድቃን ጮኹ፥ እግዚአብሔርም ሰማቸው፡፡" ***መዝ 34፡15 እና 17፡፡***

# <u>አማላጅነት</u>

3. ***በሰማይ ያሉ ቅዱሳን አምልኮተ እግዚአብሔርን በመፈጸም ተጠምደው አይረሱንም?***

- **በሰማይ ያሉት ቅዱሳን** "እንደ ደመና በዙሪያችን ያሉ ምስክሮች ናቸው፡፡" <u>*ዕብ 12፡1፡፡*</u> **ቅዱስ ዮሐንስ** "መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፥ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።" <u>*ራዕ 5፡8*</u>፣ "የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።" <u>*ራዕ 8፡4*</u> **ይላሉ፡፡ በሲኦል የነበረው ነዌ እንኳ በሲኦል ሆኖ ዘመዶቹን ያልረሳ ቅዱሳኑ ይረሳሉ?** <u>*ሉቃ 16፡21-31*</u>፡፡ **ያረፉት በምድር የሚሆነውን ተመልክተው** "በታላቅ ድምፅም እየጮኹ። ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ።" **ከማለት መቼ ተከለከሉ?** <u>*ራዕ 6፡10፡፡*</u>

4. **በዓለም ከ1 ቢለዮን በላይ ካቶሊኮችና ከሦስት መቶ ሚሊዮን በላይ ኦርቶዶክሶች አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል አንድ ፐርሰንት ያህሉ እንኳ የእመቤታችንነ ጸሎት ቢጸልዩ እመቤታችን 130000 ጸሎት በየቀኑ ትቀበላለች ማለት ነው፡፡ ታዲያ ለዚህ ሁሉ ጸሎት መልስ ለመስጠት ጊዜ እንዴት ትችላለች?**

- **በሰማይ ያለው የጊዜ አቆጣጠር በምድር እንዳለው አይደለም፡፡ ጥያቄው አሁንም መቆጠር የሚችል (Finite) ነው፡፡ ስለዚህ ተቀባዩም መወሰን ያለው ስጦታ ብቻ ይበቃዋል፡፡ ይህንም እግዚአብሔር በሰማይ ላከበራቸው ነፍሳት ሰጥቷል፡፡ በ** Internet chat room **ከ50** በላይ የሆኑ ሰዎች በዓለም ዙሪያ ከሚገኙት ጋር በአንድ ጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡፡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሰው ይህን ማድረግ ከተቻለው እግዚአብሔር ደግሞ "እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናስበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ የሚቻለው ነው፡፡" <u>*ኤፌ 3፡20፡፡*</u>

- **ቅዱስ ጴጥሮስን በአንድ ጊዜ ትምህርቱ ሦስት ሺ ነፍሳትን እንዲማርክ ያስቻለው እርሱ ለምትለምነው ነፍስ ሁሉ እንደ ልመናዋ በቅዱሳኑ መመለስ ይቻለዋል፡፡** <u>*የሐ ሥራ 2፡፡*</u>

- **በዮሐ 11፡26፡፡ ጌታችን** "ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም።" **ብሎናል፡፡**

ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡